የሰ.መ.ቁ 61788

ሰኔ 14 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለማ

**ተጠሪ፡-** ታፈሰ ተሰማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን ፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተደረገውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሃዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ሲሆን ፣ ፍ/ቤቱ በሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከተመለከተ በኋላ የንብረት ክፍፍሉ በዕጣ እንዲሆን በማዘዝ አከፋፍሎአል በወጣው ዕጣ መሠረት ለአመልካች የደረሰው ቤት ለተጠሪ ከደረሰው ቤት በዋጋ የሚበልጥ ነው በማለትም አመልካች ብር 31,585.65 ለተጠሪ ትክፈል ብሎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሣኔው ባለመስማማት ለሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን ፣ ችሎቱ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የንብረት ክፍፍሉ የተመራው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለክፍፍል የቀረቡት ንብረቶች በፍቺ የተለያዩት ባልና ሚስት /ተከራካሪዎች/ የጋራ ሃብት ናቸው፡፡ ከዚህ ደግሞ በቅድሚያ መገንዘብ የሚቻለው ሁለቱም በሃብቶቹ ላይ እኩል የሆነ መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመብት ረገድ አንደኛው ከሌላኛው አያንስም ወይም አይበልጥም ከተባለ ደግሞ የክፍፍሉ ሥርዓትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው

መከናወን ያለበት፡፡ የእኩልነት መርሁ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35/1/ እና/2/ የተቀመጠ ሲሆን ፣ ቀጥለው በወጡት የፌዴራል እና የክልል ቤተሰብ ሕጎችም እንደዚሁ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የቤተሰብ ሕግ "የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 " ሲሆን የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ለሁለቱም እኩል እንደሚከፋፈል በአንቀጽ 101/1/ ደንግጎአል፡፡ በእርግጥ ባልና ሚስቱ ሃብታቸውን በስምምነት ለመከፋፈል ከፈለጉና ከቻሉ ሕጉ ይህን ስምምነታቸውን እንደሚያከብርላቸውም ተመልክቶአል፡፡ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ በስምምነት መከፋፈል ካልቻሉ/ካልፈለጉ / የክፍፍሉ ሥርዓት እንዴት ሊከናወን ይችላል? የሚለው ነው፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሰው የቤተሰብ ሕግ የክፍፍል ሥርዓቶቹን በቅደም ተከተል በዝርዝር አስቀምጦአል /በአንቀጽ 102/2/ እና በአንቀጽ 103/1/ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በአይነት ሊከፋፈሉ የሚችሉ ናቸው አልተባለም፡፡ ችግሩ የተፈጠረው በአይነትም ለመከፋፈል ሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ ባለመድረሳቸው ነው፡፡ አመልካች እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ እየተከራከረች ያለችው በእጣ ደርሶሻል የተባልኩት ከስምምነቱ ውጪ ነው፡፡ በዕጣ የደረሰኝ ነው የተባለውን ንብረት ብወስድ እጎዳለሁ፡፡ ተጠሪ አልተጎዳሽም የሚል ከሆነ ለኔ ደርሶአል የተባለውን ንብረት ብር 31,585.65 በመክፈል ጠቅልሎ ይውሰድ ፤ እኔ ደግሞ ለእሱ የደረሰውን ልውሰድ በማለት ሲሆን፣ ተጠሪ ግን በዚህ አይስማማም ፡፡ እየተከራከረ ያለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ነው፡፡ ከዚህም በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው በንብረት ክፍፍሉ ግራ ቀኝ ወገኖች አለመስማማታቸውን ነው፡፡ እጣ እንዲወጣ ያዘዘውም ፍ/ቤቱ /በራሱ አነሳሽነት / እንጂ ተከራካሪ ወገኖቹ ክፍፍሉ በዕጣ ይሁን ብለው ስለተስማሙ እንዳልሆነም ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት ጭምር ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ፍ/ቤቱ ወደ ዕጣ አማራጭ የሄደው ግራ ቀኝ ወገኖች በስምምነት ለመከፋፈል ባለመቻላቸው እና ንብረቱም በአይነት የማይከፋፈል በመሆኑ እንደሆነ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰጠው ውሣኔ ተመልክቶአል፡፡

በንብረቱ ክፍፍል ረገድ ችግር ሲያጋጥም ማለትም ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን እንዲከፋፈል እንደሚደረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 103/1/ ግልጽ ባለሁኔታ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ድንጋጌ ንብረቱ በዕጣ የሚከፋፈልበትን የክፍፍል ሥርዓት በአማራጭ አላስቀመጠም፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ከሕጉ በመውጣት ውሣኔ መስጠት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ሕጉ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው /አንቀጽ 103 / ቀደም ሲል የተመለከትነውን የእኩልነት መርህን ግንዛቤ ውስጥ በማግባት እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመሆኑም የንብረቱ ክፍፍል በዕጣ እንዲሆን በማለት የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የሃዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ 20692 በ28/10/2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፣ የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 08513 በ8/11/2002 ዓ.ም የሰጠው

ትዕዛዝ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ 44349 በ27-1-2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች እና ተጠሪ ንብረቱን መከፋፈል ያለባቸው በቤተሰብ ሕጉ በተዘረጋው የክፍፍል ሥርዓት መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ